# በወልቃይት የአማርኛ ዘፈን በመዝፈኑ የታሰረው ወጣት እንዲፈታ የጠየቁት ክስ እንደተመሰረተባቸው ገለፁ

~ ከተፈቱት የወልቃይት ኮሚቴ አባላት ጋር በተገናኘም ክስ ቀርቦባቸዋል
~"ቀድመው ክስ የሰጡን ፈርተው ይሰደዳሉ ብለው ነው፣ በእኛ ክስ ሕዝብን ለማስፈራራትም ነው" ተከሳሾቹ
**(በጌታቸው ሺፈራው)**

የፌደራል አቃቤ ሕግ ትግራይ ቅርንጫፍ ወልቃይት ልዩ ቦታው አዲረመጥ ከተማ የአማርኛ ዘፈን ዘፍኗል ተብሎ ስለታሰረ ወጣት ጠይቀዋል የተባሉ 9 ግለሰቦች ክስ ተመሰረተባቸው። ግለሰቦቹ ከእስር ከተፈቱት የወልቃይት አማራ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴ አባላት ጋር በተገናኘም ክስ ተመስርቶባቸዋል። የካቲት 2/2010 ዓም በተፃፈው የክስ ማመልከቻ፣ በእነ ፈረደ እሸቱ ክስ መዝገብ ስር የተከሰሱት 9 ግለሰቦችን በቅርቡ ከእስር ከተፈቱት ኮ/ል ደመቀ ዘውዱ፣ አታላይ ዛፌ፣ መብራቱ ጌታሁን፣ ጌታቸው አደመ፣ ጎይቶም አማረ እና ሁመራ ታስሮ በ2009 ዓም ከእስር ከተፈታው ዘነበ ተስፋዬ የተባለ ግለሰብ ጋር በተገናኘ ክስ ተመስርቶባቸዋል።



በወልቃይት የአማራኛ ዘፈን በመዝፈኑ የታሰረውን የአማራ ወጣት እንዲፈታ በመጠየቃቸው የታስሩ አምራ ወጣቶች

በእነ ፈረደ እሸቱ አበጋዝ ክስ መዝገብ ክስ የተመሰረተባቸው ፈረደ እሸቱ አበጋዝ፣ አባይ ማማይ እጅጉ፣ ደሞዜ መልኬ ሰጥአርገው፣ ክብረአብ ስማቸው የሸወንድም፣መምህር ፈረደ በሪሁን ቢያድጎ፣ ታምራት ደሳለኝ ደርሶ፣ መምህር እንዳለው ብርሃኔ ገ/ማርያም፣ መምህር ሞላ አበለይ በላይ እና መምህር ልዑል ሐጎስ ገ/እግዚያብሔር ናቸው።
በእነ ፈረደ እሸቱ ላይ 6 ክሶች የቀረበባቸው ሲሆን ዘነበ ተስፋዬ "ለምን ታሰረ፣ አማራ በመሆኑ ነው የታሰረው" ብለው እንደጠየቁ፣ ጎይቶም አማረ የተባለ የኮሚቴ አባል በአማራነቱ ነው የታሰረው ማለታቸውን፣

ወይቃይት የአማራ ነው እንዲሁም ትግራይ ተከዜ ማዶ ነው ብለዋል ሲል የክስ ዝርዝሩ ላይ ተጠቅሷል። የሚሊሻ አባል በሕዝብ ላይ እርምጃ እንዳይወስድ ነግረውታል የሚል ክስም ቀርቧል። ከዚህም በተጨማሪ በ6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች ላይ "የማንነት ጥያቄያችን የማትመልሱልን ከሆነ አንቀፅ 39 መሰረዝ አለበት" ብለዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል።
ዘነበ ተስፋዬ የተባለ ወጣት ወልቃይት አዲረመጥ ላይ የአማርኛ ዘፈን በመዝፈኑ እንደታሰረ፣ በወቅቱም የከተማው ሕዝብ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ቀርቦ እንደነበር የተገለፀ ሲሆን ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ወጣቶቹ ከ150 እስከ 300 የሚሆን ሕዝብ ቀስቅሰው ስብሰባ አድርገዋል የሚል ክስ መስርቷል።
በግለሰቦቹ ላይ የቀረቡት 5 ክሶች "ወልቃይት የአማራ ነው በማለት የሕዝብ አንድነትን በመሸርሸር" የሚል ሲሆን 4ኛ ተከሳሽ ክብረአብ ስማቸው በ2008 ዓም ከኮ/ል ደመቀ ዘውዱ፣ መብራቱ ጌታሁን፣ አታላይ ዛፌ እና ጌታቸው አደመ ጋር በመገናኘት ከኮ/ል ደመቀ ዘውዱ እጅ 20 ሺህ ብር ተቀብሎ ለሽብር ዝግጅት አርጓል በሚል በፀረ ሽብር አዋጁ አንቀፅ 4 ስር ተጨማሪ 4ኛ ክስ ቀርቦበታል።

## የካቲት 2/2010 ዓም የቀረበው

ክስ ተከሳሾቹ ከአሁን ቀደም በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቀሌ ቅርንጫፍ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቶ እንዳልቀረቡ ይገልፃል። ሆኖም ተከሳሾቹ ከዚህ በፊት ምንም አይነት ክስ እንዳልደረሳቸው ገልፀዋል። አሁን የቀረበባቸው ክስ በሁመራ ከተማ የመቀሌ ተዘዋዋሪ ችሎት እንዲቀርቡ ለሚያዚያ 5/2010 ዓም ቀጠሮ ይዟል።
"ወልቃይት ውስጥ ድንገት አፍኖ ከማሰር ውጭ ቀድሞ ክስ መስጠት የተለመደ አይደለም" ያሉት ወጣቶቹ "ቀድመው ክስ የሰጡን ፈርተው ይሰደዳሉ ብለው ነው፣ በእኛ ክስ ሕዝብንም ለማስፈራራት ነው" ሲሉ ገለፀዋል።